# <u>ትብብር ከማን ጋር? ዓላማውና ልዕለ-ግቡስ?</u>

## ኢትዮጵያን ለማዳንና ሕዝቧን ለመታደግ ኢትዮጵያዊ አስተሣሰብንና እምነትን ይጠይቃል!

*(ክፍል አራት - ካለፈው የቀጠለ)*
*ከአያልሰው ደሴ፦ የግል አስተያየት (ሚያዝያ ፳፺ ቀን ፪ ሀሽ ፫ ዓ/ም)*

ይኸ ጉዳይ ለአንዳንድ ወገኖች "የማይመች ወይም የማይጥም ሃቅ" መሆኑን ባላጣውም ከየግላችን በላይ የሆነችውን የጋራ አገራችንን የሚመለከት ስለሆነ እውነቱን በግልጥ መነጋገሩ ግን አስፈላጊ ነው እላለሁ::

**አንድ ግልጥ ሣይሆን ማለፍ የሌለበት ጉዳይ እነኝኸ ኃይሎች ያላቸው ፀረ-አንድነትም ይሁን የመገንጠል ዓላማ ሲወሣና ከነሱ ጋር የሚደረግ መተባበር ቢያንስ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል ሲባል የሌላቸውን ኃይል እንዳላቸው ተቆጥሮም ሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአንድነቱ ያለውን ከፍተኛ ቀናዒነት አኮስሶ በማየት የግድ እነሱ እንደሚመኙት ይሆናል ማለትም አይደለም:: በዚያው ልክ ያ ምኞታቸው እንደ በረሃ ውልብልቢት ወይም ምናብ የማይጨበት ግብ ነው ማለትም አይቻልም:: ከእኔው ጀምሮ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያውያንን የሚያሣስበን ግን አስቾጋሪና ተግባራዊነቱ አጠራጣሪ ከሆነው የግባቸው እውን መሆን-አለመኑ ይበልጥ፣ በቅድሚያ በትጥቅ ትግል ተፈጻሚ እንዲሆን የያዙት ፍልሥፍናና አሠላለፍ በንፁኃን ሰላማዊ ዜጎች እና በአገሪቱ ላይ የሚያስከትለውን ደም-መፋሰስ፣ ትርምስና ሰቆቃ፣ በሕዝባችን የፍትኅ፣ የእኩልነትና የአንድነት ትግል ላይ የሚያደርሰውን እክልና አሉታዊ ሚና ግምት ውስጥ በማስገባትና ያም እየተገዘገዘ ባለው የኅብረተሰባችን ትሥሥር ላይ የሚያስከትለውን አደጋ እንዲሁም ከዚኹ ጋር ተያይዞ "ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል" እንዲሉ አገራችንን ለማዳከምና ለመበተን ዓልመው ለተነሱ ክፍሎች አመቺ ሁኔታን ሊፈጥር የመቻሉና ለአካባቢው ሰላምና መረጋጋት እጦት የሚኖውን አሣሣቢ አስተጋብዖ በማሰብ ጭምር ነው:: በተጨማሪ መረሣት የሌለበት ጉዳይ ጥቂቶችን በአባልነት ያቀፉ ታጣቂ ቡድኖች ዕድሉን ካገኙና በአንድ አካባቢ እግራቸውን የመትከል አመቺ አጋጣሚ ከተፈጠረላቸው፣ "እንወክለዋልን፣ ቆመንለታል" በሚሉት ሕዝብ ላይ ፍላጎታቸውን በጉልበት ለማስፈጸም እንደሚችሉ በተደጋጋሚ የታየና የተረጋገጠ ሃቅ መሆኑን ነው:: ስለሆነም ነው አሁን የተያዘው ዓይነት "ትብብር" እነዚኸን ታጣቂ ቡድኖች እግር እንዲተክሉ ከማስቻል ውጭ አዎንታዊ እርባና የሌለው:: ያ ሲሆን ደግሞ ለዚያ የምታበቋቸው "የአንድነት" ክፍሎች ከወዲኹ ምንም "ቃል ይግቡ" ምን በነዚኹ ኃይሎች ላይ ምንም ዓይነት ቁጥጥርም ሆነ ጫና ልታደርጉ አችሉም የምለው፤ ጥረቱም እነዚኸኑ ቡድኖች ኮትኩቶ ከማሳደግና አንከባክቦ ወደ-ግባቸው አድራሽ ከመሆን ውጭ የማይሆነው::**

ከዚኹ ጋር በተያያዘ ሌላም በማያሻማ መንገድ ግልጥ መሆን ያለበት ጉዳይ ያለ ይመስለኛል:: ይኸም በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ እነዚኸን ጠባብ ቡድኖች "ቆመንለታል" ለሚሉት ሕዝባችን "ሕጋዊ" ተወካይ እንደሆኑ አድርጎ ማየትን በተመለከተ ነው:: አዎን ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት በልዩ ልዩ አስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት በእነኝኸ ቡድኖች ሥር የተሠለፉ ወገኖቻችን ጠላቶቻችን አይደሉም:: በአንፃሩ በእነዚኸ ቡድኖች ሥር የተሠለፉ ወገኖቻችን የአንድነት ኃይሉን እንደ-ጠላት ቢያዩት ሊገርም አይገባም:: ምክንያቱም የቡድኖቹ ትምሕርትና ዓላማው እራሱ በአባላቱ ዘንድ የአንድነት ክፍሉን (የቀረውን ኢትዮጵያዊ ወገኑን) "መጥፋት/መውገድ" ያለበት አውሬ ተደርጎ እንዲታይ የሚያደርግ ሥነ-ልቦናን የሚቀርፅ ስለሆነ ነው:: በእርግጥም ያ የእነሱ ህልም እውን መሆን የሚችለው ጠላት ተደርጎ በተፈረጀውና በሚታገሉት ኢትዮጵያዊነት/ አገራዊ አንድነት መቃብር ላይ ብቻ ነው::

በተወሰነ ቡድን አማካይነት በአንድ አካባቢ በሚኖር ሕዝብ ስም የመገንጠል ጥያቄ መነሣቱ ብቻ ጥያቄውን ፍትኃዊም ሆነ ወይም "በመሬት ላይ ያለ እውነታ" ስለሆነ ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል ማለት አይደለም:: በአብዛኛው ጥቁር አሜሪካኖችን "ባሪያ" አድርው እንደ ሰው ሣይሆን እንደ-ንብረት ይዘን የመቀጠል መብታችንን ከምንቀማ ተገንጥለን ነፃ መውጣት አለብን በሚሉ ክፍሎች አሜሪካ ለአሰቃቂ "የሰሜንና የደቡብ" የእርስ-በርስ ጦርነት የተዳረገችው ያን የመገንጠል ጥያቄ ያቀረቡ የተወሰኑ ቡድኖችን አጉል ጥያቄ መቀበል ስህተት በመሆኑ ነው:: ያ በጊዜው በነበረው መንግሥት አማካይነት የተደረገና በተገንጣዩ ክፍል ላይ ድልን የተቀዳጀ ትግልም ውጤቱ ያ አስከፊ ኢ-ሰብዓዊ ሥርዓት እንዳይቀጥል ማድረግ ብቻ ሣይሆን ሊገነጠል የተነሣውን ክፍል ጨምሮ ለጠቅላላው የአሜሪካ ሕዝብ መረጋጋትን፣ ሰላምንና ብልጽግናን አስገኝቷል::

የመገንጠልን ጥያቄ ስንቃወም አንዳንዶች ጉዳዩን ለማድበስበስ ሊያቀርቡት እንደሚከጅሉት እነዚኸ ቡድኖች "ነፃ" እናወጣለን የሚሏቸውን ወገኖቻችንን በአንድነት ስም "ያለፈውን እንበለ-እኩልነት ሥርዓት" ለመመለስ፣ መብቶቻቸውን ለማፈንና ያለ-ፍላጎታቸው ተረግጠው እንዲገዙ ለማድረግ እንዳልሆም ሊታወቅ ይገባል:: ያ የትግላችን ታሪክ የሻረው ከንቱ ክርክር ነው:: ችግራችን

ድርጅቶቹ ከቆሙበት ፀረ-ኢትዮጵያ ዓላማና ያንን ተግባራዊ ለማድረግ ከሚከተሉት ልዩነቶችን ከሚያካርርና ከሚያሠፋ፣ በኅብረተሰባችን መኻል እየቆየ የሚያመረቅዝ የብቀላ አዙሪትን ከሚወልድና የውጭ ኃይሎችን ጣልቃ-ገብነት ከሚጋብዝ በኃይል የተደገፈ የትግል መሥመር ላይ ነው:: የአንድነትና የዴሞክራሲው ኃይል የእነኝኽን ቡድኖች የመገንጠል/ፀረ-አንድነት አቋም ሲቃወም የነሱ ዓላማ በወል መብት ስም የእያንዳንዱን "ነፃ" ይውጣ የተባለ ግለሰብ ወገናችንን ሰብዓዊ መብቶች መስዋዕት የሚያደርግ፣ ሲበዛ በጠበበ መልኩ ወገንተኛና "በልዩነት" ተቻችሎና ተከባብሮ መኖርን የማያስችል አስተሣሰብ በመሆኑ፣ በሁላችንም ጥቅሞች፣ በሰላም፣ በመረጋጋትና በሁሉም የወደ-ፊት የጋራ ተስፋ ላይ አሉታዊ ውጤትን ስለሚያስከትል ነው::

ለሁሉም የጋራ ጥቅምና መብቶች መከበር፣ ለተሻለ እኩልነትና ለፍትኅ የቆመውና የሚታገለው የአንድነትና የዴሞክራሲው ኃይል በታጠቀ ኃይል የተደገፈን የመገንጠል አቋም/ዓላማ ሲቃወም በልዩ ልዩ አስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት ወደ-እነዚኽ ድርጅቶች የተቀላቀሉ ወገኖችን ጠላት አድርጎ አያይም፤ መቀላቀላቸውም በራሱ ወንጀል አይደለም:: ሁሉም ሊረዳ የሚያስፈልገው ሃቅ ደግም ለእያንዳንዱ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ጠላት አድርጎ በመፈረጅ የመገንጠል ዓላማን ያነገበ የኦብነአግ አባል፤ የጋራ ተስፋን ሰንቀው፣ ለውድ አገራቸው ለኢትዮጵያ አንድነትና ብልፅግና፣ ለተሻለ እኩልነትና ፍትኃዊ ሥርዓት ጠብቀው የሚታገሉና በሕይዎታቸው ጭምር መስዋዕትነት የከፈሉና የሚከፍሉ በመቶ ሽህዎች የሚቆጠሩ የአካባቢው (የኦጋዴን) ተወላጅ ወገኖቻችን እንዳሉ፤ ለእያንዳንዱ በተመሣሣይ ፀረ-አንድነት ዓላማ የተሰለፈ የኦነግ አባል ይኽችን አገር የተሻለ እኩልነት የሚረጋገጥባት፣ ፍትኅ የሰፈነባት እንድትሆን፣ ለሁሉም ዜጎቿ ዕድገትና ብልፅግና የቆሙ፣ አንድነቷን በቀናዒነት የሚመለከቱ፣ አቅፈው ደግፈው ያስከበሯትና ሊያስከብሯና ኮርተው ሊያኮሯት የተሰለፉ በብዙ መቶ ሽህዎች የሚቆጠሩ ኦሮሞዎች እንዳሉ ነው:: ስለሆነም ከእነዚኽ ቡድኖች መወገንም እነኝኽን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኦሮሞዎችና ኦጋዴናውያን ኩሩ የኢትዮጵያ ልጆች ፍላጎት መጋፋትና መፃረር እንደሚሆንም ያስተውሏል:: ሲያልፍም ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ ያሰኙ፣ ለአንድነቷና ለክብሯ ክቡር ሕይዎታቸውን አሣልፈው በሰጡና አሁንም ከነሱነታቸው ነጥለው ለማያዩዋቸው ለአገራቸው ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት፣ ለማይነጣጠል የጋራ ዕጣ-ፈንታና አብሮነት በቆሙ ኦሮሞዎችና ኦጋዴናውያን መሣለቅ ይሆናል::

የሆነ-ሆኖ ይኽ አጓጉል አካሄድ በዴሞክራሲያዊ የአንድነት ኃይሎች አገር-አቀፍ የጋራ ትግል፣ በሕዝባችን የጋራ ጥቅሞችና በውድ አገራችን አንድነት ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ገጽታ እናቆይና ለነዚኽ አዲስ "ትብብር" ፈጣሪ ፀረ-አንድነት ኃይሎች የሚያስገኝላቸውን ጥቅም በአጭሩ ማየቱ አስፈላጊ ይመስለኛል:: ይኽ ሂደት ለእነዚኽ እስከ-አሁን ድረስ ከመቀመጫቸው መነሣት ላቃታቸውና በየጊዜው እየተገመሱ፣ እየሟሸሹና እየኮሰመኑ ለመጡ ኃይሎች ዓላማችን ብለው ላነገቡት ግብ የሚከተሉትን የማይናቅ አስተዋፅዖ ሊኖራቸው የሚችል ተደጋጋፊና ተያያዥ ጥቅሞችን ያስገኝላቸዋል ማለት ይቻላል::

ሀ) እነኝኽ ቡድኖች ከሌሎች በኢትዮጵያ ስም ካሉ ድርጅቶች ጋር ቆመናል ሲሉ ወዲያውኑ የሚያስገኝላቸው ጥቅም አለ:: ይኽ "አዲስ አቋም" በተለይም ባለፉት ጥቂት ዓመታት የውስጥ ትርምስ የገጠማቸውና በየጊዜው የመፈረካከስ አባዜ ያጠቃቸውን እነኝኽ ቡድኖች "ከተደበቁበት" ወደ-አደባባይ ሊያወጣቸው፣ በደጋፊዎቻቸው ብቻ ሣይሆን ከዚያም ውጭ ባሉ ክፍሎች የተሻለ "ተደማጭነት" እና "ተቀባይነት" ሊያተርፍላቸው፣ ስማቸውንም "ሊያድስላቸው" መሰባሰብንም ሊያስገኝላቸው ይችላል:: የገንዘብ እርዳም ከዚሁ ጋር የሚመጣ ሌላው የአጭር ጊዜ ጥቅም ነው:: ስለሆነም ይኽ ድርጊት ለነኝኽ "የታፈኑ" ቡድኖች አየር-አቀባይና ነፍስ-ዘሪ ነው ማለት ማጋነን አይሆንም::

ለ) ሌላው ጥቅም የሕዝብ መነሣሣት አየር በሚነፍስበት በአሁኑ ጊዜ የእነዚኽ ቡድኖች የሌላቸውን ኃይል አጉልቶ በሚያሣይ መልክ እንደዚኽ ብቅ-ብቅ ማለት የሕዝብ መነሣሣት ስጋት የሚያባንነው የመለስ አገዛዝ አፈናውን በተለይም እነዚኽ ክፍሎች "የእኛ" በሚሏቸው አካባቢዎች ላይ ልዩ ትኩረት እንዲያደርግና ሕዝቡን ለባሰ ችግርና መፈናቀል ለሚዳርግ ዘመቻ ሊዳርግ ይችላል:: አለኝታ የሚሆንና ታግሎ የሚያታግል ሁነኛ ብሔራዊ አማራጭ በሌለበት ሁኔታ ይኽንን የሕዝብ መነሣሣትና ሰላማዊ አመፅ "አደጋ" አስቀድሞ ለመከላከል አገዛዙ ሊወስድ በሚችለው አዲስ የአፈና እርምጃ ምክንያትም የየ-አካባቢው ሕዝብ ሌላ መሄጃ አማራጭ በማጣትም ጭምር እንዲሁም የአገዛዙ በጉልበት የታጀበ ስቃይ፣ አፈና፣ ግድያ፣ ወዘተ.. በቀጥታ በሱነቱ (ኦሮሞ በመሆኑ፣ ኦጋዴናዊ በመሆኑ) ብቻ የተዘመተበት መስሎ ስለሚገኝ፣ ሳይወድም ቢሆን ወደ-እነዚኽ በስሙ በሚንቀሣቀሱ ድርጅቶች ማየት የሚገደድበት ሁኔታ ስለ-ሚኖር፣ ለቡድኖቹ መቆናጠጫ የሚሆን ድርጅታዊ መረብ ለመዘርጋት የሚያስችል የተሻለ አጋጣሚን ሊፈጥርላቸው ይችላል:: ያ ግን ወደ-ኋላ እንደምናየው ግልጥ የሆነ አሉታዊ ገጽታ አለው::

ሐ) እነኝኸ ቡድኖች በኢትዮጵያ ስም ከሚንቀሣቀሱ ድርጅቶች ጋር “ተባብረን” እንንቀሣቀሣለን ሲሉ ከሚያተርፍላቸው የተሻለ ወጥቶ የመታየት ጥቅም ተያይዞ እነሱ “እንወክለዋለን” ለሚሉት አካባቢ ሕዝብ “ሕጋዊ ተጠሪ”፣ እየቆየም “ብቸኛ ተጠሪ” ሆነው እንዲቀርቡና በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሜዳ ላይ የተሻለና አልፎም የሕዝቡን ትክክለኛ ስሜትና ፍላጎት ሊፃረር የሚችል ያልተመጣጠነ “እውቅና” ማግኘት ሌላው ዕድል ነው:: በመስክ ላይ መቆናጠጥ ሲችሉ ደግሞ በዚያ “የእኔ” በሚሉት አካባቢ እንደ ግንቦት-ሰባት ዓይነት አገር-አቀፍ ነኝ የሚል ድርጅት ኅልውና ሊኖረውና ሊንቀሣቀስ አይችልም:: ሕወሓት/ወያነ ኢሕአፓና ኢድኅ ትግራይ ውስጥ “ቦታችሁ አይደለም” እንደተባሉት ማለት ነው:: በተጨማሪም አብረዋቸው የቆሙ “ኢትዮጵያውዊ” ድርጅቶችን ተመርኩዘው ባገኙት በዚኸ የተሻለ ኀልቶ መታየት፣ ፍትኀንና እኩልነትን በአገሪቱ ላይ ለማስፈን በሚደረገው አገር-አቀፍ ጥረትም ይሁን በማንኛውም የመሸጋገሪያ ሂደት ላይ አሁን ባሉበት ሁኔታ ሊያገኙት የማይችሉትን ያልተመጣጠነ “ተፈላጊ ሆኖ” የመገኘትና በአገሪቱ መፃዒ ዕድል ላይ የበለጠ የመወሰን አቅምን ሊያተርፍላቸው ይችላል:: ያ ደግሞ በቀጥታ ሲተረጎም ቢያንስ ቢያንስ የመለስ ዜናዊ ፖለቲካዊ ኅሠኝነትን መሠረት ያደረገ ሥርዓት በተረጋገጠ መልኩ እንዲቀጥል ይሆናል ማለት ነው::

መ) ይኸ “ትብብር” የሚያስገኝላቸው ሌላው ጥቅም በአገር ውስጥ በተለይም “የእኛ” በሚሏቸው አካባቢዎች ከዚያም በዓለም-አቀፍ ማኅበረሰቡም የተሻለ እውቅናን ሊያተርፍላቸው ይችላል:: ያ ደግሞ ከላይ የተጠቀሱ መዘዞችን ከማከተሉ ሌላ በተራው በ“ሦስተኛ ኃይሎች” አማካይነትም ይሁን አገዛዙ በራሱ ለራሱ ሲል ከነሱ ጋር እንዲደራደር አዲስ አቅም ይፈጥራላቸዋል:: ይኸ ደግሞ ተቃዋሚ የሚባለውን ጎራ ለመፈረካከስ አገዛዙ ሊጠቀምበት ስለሚፈልግ የሚደረግ ብቻ ሣይሆን በሁለቱም በኩል የፍልሥፍና አንድነት ስላላቸው መሆኑ ሊገርም የማይገባና ይሆናል ተብሎ ሊጠበቅ የሚገባው ጉዳይ ነው:: አሁን ከነሱ ጋር ለመተባበር ደፋ-ቀና የሚሉና ጊዚያቸውን የሚያጠፉ ወገኖችንም እነዚኸ ከሙት ያነሷቸው ቡድኖች ይበልጥ ሊያምኑት ከሚችሉትና ስትራቴጂያዊ አጋራቸው ከሆነው ከሕወሓት/ኢሕአዴግ ጋር ሊታረቁበት የሚያስችል አዲስ የመደራደሪያ ጉልበትን ሲያገኙ ከአንድነት ኃይሉና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አቃቅረዋቸውና ዞር-ብለውም ሣያዩአቸው በቁም ገትረው ወይም “አስደግፈው” ይተዋቸዋል ማለት ነው:: ሁለት ጊዜ ሞት ይሏል ያ ነው::

የተባለውን “ትብብር” ከሚያራምዱና ይኸንኑ “ጥረት” ከሚደግፉ ወገኖች ወደ-ሚቀርቡ የማሣመኛ ነጥቦች ስንዞር ደግሞ፤

ሀ) *“ዓላማችን ወያኔን ለመጣል ስለሆነ ከማንም ጋር መተባበር ይገባል”*፡- ይኸ አባባል የራሣችንን የቅርብ-ጊዜ ታሪክ ጨርሶ የዘነጋ፣ የነዚኸን ኃይሎች መሠረታዊ ዓላማ ያልተረዳ፣ በአገራችን ያለውን የኃይል አሠላለፍ ስሌት ውስጥ ያላስገባ፣ ትግሉ በነጠላው ከሕወሓት/ኢሕአዴግ ጋር ሣይሆን እሱ ከቆመበት ሥርዓት ጋር መሆኑን ያላገናዘበ እና ድኅረ-ሕወሓት/ኢሕአዴግ ስለ-ሚኖረው በጥንቃቄ መታየት ስለሚኖርበት አስቸጋሪ ሽግግር ራቅ-አድርጎ ያላየ ግልብ አስተሣሰብ ላይ የተመሠረተ ነው:: ይኸ ደግሞ በጥሬው ሲወሰድ “ከወያኔ የባሰ አይመጣም” ከሚል “ቀና” አመለካከት ሊመነጭ ይችላል:: ይኸ የተዛባ ግንዛቤም አንዳንድ ወገኖችን፣ ጠንካራ አገር-ወዳዶችን ጭምር አጉል ቦታ ላይ ሲጥል አይተናል:: በዚኹ “*ወያኔን ብቻ እንደ-ምንም እናስወግድ*” አስተሣሰብ በመመራትም የተወሰኑ የአገራቸው ጉዳይ እንደ-ውስጥ እግር እሣት የሆነባቸው አገር-ወዳዶች ሣይቀሩ ሸዓብያን ከመሰሉ የለየላቸው ፀረ-ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እንደ-ሬት ከሚያንገፈግፋቸው ክፍሎች “የትግል ሜዳቸውን” አሥመራ አድርገው ወርቃማ ጊዚያቸውን ሲያባክኑ በቁጭት ተስተውሏል:: (በዚኸ ጉዳይ ላይ ቀደም-ሲል “*ከራሱ ጋር መታገልን ያላወቀበት ተቃዋሚ ጠላቴ የሚለውን ለማቸነፍም ይሁን የቆመለትን ግብ እውን ለማድረግ ተስፋ አይኖረውም! ከኢሣኢያስ ጋር ቆሞ ለኢትዮጵያ ነፃነት?! ኧረ እየተስተዋለ፣ ወገን!!*” በሚል ርዕስ በቀረበ ጽሑፍ ላይ የጉዳዩን አሳሳቢነት ለማስገንዘብ ስለ-ሞከርኩ እዚኸ ላይ አልደግመውም:: (here)

በደርግ አገዛዝ የተማረሩና የሱንም መውደቅ የፈለጉ ኢትዮጵያውያን *“በጋራ ጠላት ላይ ያለን የትግል አጋርነት”* ለማሣየት በመፈለግና በዚኸ በቀጭኑ የተተረጎመ “*የጠላቴ ጠላት*” ስሌት በሸዓብያ ስብሰባዎች ላይ በመገኘትም ይሁን ለዝግጅቶቻቸው በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እርዳታ ማድረጋቸው ውጤቱ አገር አትገነጣጠልም፣ የኤርትራ ወገናችንም ኢትዮጵያዊነቱን አይጣ፣ ወዘተ.. ብለው ለአገራቸው ክብር የተሠለፉ ወገኖችን መግደያና የኢትዮጵያን አንድነት ማፍረሻ ለሚሆን ጥይት መግዣ አስተዋፅዖ እንዳደረጉ በጊዜው አልተገነዘቡትም:: አሁንም ቢሆን ማንኛውም በፖለቲካ ፍልሥፍናውና በአቋሙ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆነ ቡድን ዝግጅት ላይ በመገኘት የዚያን ድርጅት አቋም ማስቀየር የሚቻል የሚመስላቸው፣ ወይም መገኘቱ “ወደ--መኻል” እንዲመጡ ሊያደርጋቸው ይችላል፣ “የባሰ እየራቁ እንዳይሄዱ ይረዳል” የሚል እምነት ያላቸው ወገኖች አጋጥመውኛል:: እነዚኸ ወገኖች ያልተገነዘቡት ሃቅ ግን በነሱ ዝግጅት “የሌላው” መገኘትና ተሣታፊ መሆን ለነሱ

የተሻለ የሞራል ድጋፍን የሚሰጣቸው፣ ምናልባትም ዓላማቸው ትክክልና ተቀባይነት ያለው ነው የሚል የተሣሣተ መልእክት የሚያተላልፍላቸው፣ አጉል የተፈላጊነት ወይም የተደማጭነት ስሜት እንዲያድርባቸው፣ ከሚገባውም በላይ ያላቸውን ኃይል ይበልጥ አጉልተው እንዲያዩና እንዲታበዩ የሚያደርጋቸውና ቢያንስ ግን ለፀረ-ኢትዮጵያ ዓላማ የሚውል ገንዘብን መለገስ እንደሚሆን ነው:: **እንደኤ-እንደኤ እነዚኽ ኃይሎች "ወደ-መኻል" መምጣትም እንኳን ባይሆን ቆም ብለው እንዲያስቡና አቋማቸውን እንዲመረምሩ የሚያደርጋቸው ዴሞክራቱ የአንድነት ኃይል ካለፉ ስህተቶቹ ተምሮ፣ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት እምነትና መርኅ ላይ ብቻ የቆመ አደረጃጀትን ይዞ፣ አንድነቱን ጠብቆና አጠናክሮ የሕዝብ አለኝታ የሚሆንበትን አቅም እንዲያገኝ ማድረግ፣ ቢያንስ ግን በእነዚኽ ቡድኖች አጀንዳ አለመዘፈቅ ነው::**

ለ) *"ወያኔ የሚገባው ቋንቋ ኃይል ስለሆነ በተለይ ከታጠቁ ክፍሎች ጋር ተባብሮ መሥራቱ የአገዛዙን ዕድሜ ለማሣጠር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው"*:- ይኽም እንዲሁ በሌጣው ሲታይ ከሃቁ ያልራቀ አስተሣሰብ ቢመስልም፣ የዚኽ ዓይነት ትግል፣ በተለይም አሁን በሚታየው  የዚኽ ዓይነት የትግል መሥመር ሚጠይቀውን ብሔራዊ አጀንዳ ሆኖ ያለ-መቅረብ፣ የተለወጠው የዓለም-አቀፍና የአካባቢ ሁኔታ በተግባራዊነቱ ላይ የሚያሣድረው አሉታዊ ጫና፣ ባለው የኃይል አሠላለፍ ተግባራዊ ለማድረግ የሚኖረው አሉታዊነት እና በታሰበው መልክ የቆየ "ከገጠር-ወደ-ከተማ" ስልትን (አካሄድን) የመከተል ትልም ጠቃሚነቱ ይበልጥ ለአገዛዙ ሊሆን መቻሉን በተገቢ ያጤነ አይደለም:: በነዚኽ ምክንያቶችም በታሰበው መልክ በዓላማና ግብ ጨርሶ በማይገናኙ ብቻ ሣይሆን መሠረታዊ ተፃራሪነት ያላቸው እምነቶችን በአነገቡ የታጠቁና ያልታጠቁ ኃይሎች የተሰበጣጠረ አሠላለፍ ያንን ዓይነት ትግል ለማድረግ መነሣቱ ከፍተኛ ስህተት ይሆናል:: ይኽ የተሰበጣጠረ አሠላለፍና አካሄድ የሚጠቅመው ለመለስ አገዛዝ ብቻ ነው:: "ወያኔ የሚገባው ቋንቋ ኃይል ነው" በሚል ነጠላ ስሌት ከነዚኽ የለየላቸው ፀረ-አንድነትና ተገንጣይ ቡድኖች ጋር መተባበሩ ደግሞ ከመነሻው ይኽንኑ አስተሣሰብ የሚያከሽፍ ነው:: ለምን ቢሉ ማንም ኃይል ከፀረ-አንድነት ኃይል ጋር ተሠልፎ፣ ያውም ሸዓብያ በሚባል የለየለት ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይል የበላይ ጠባቂነትና በሱም ልጓም የሚነተት ታጣቂ፣ እንኳን የአገሪቱን መለዮ-ለባሽ ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ የሚያስቆጣና ከአገዛዙ ጋር መተባበርን በማያስከትል መልኩ ባለው አቅም ሁሉ እንዲፋለም የሚያደርገው ስለሚሆን ነው::  (በዚኽም ጉዳይ ላይ ያለኝን አስተያየት ቀደም-ሲል በተጠቀሰው ጽሑፍ ላይ አስቀምጫለሁ::)

ሐ) *"ትጥቅ አንስተው የሚታገሉ ኃይሎችን ምንም ጥያቄ ያንሱ ምን ቀርቦ ማነጋገሩና አብሮ መሥራቱ የበለጠ አክራሪ እንዳይሆኑ ይረዳል"*:- ይኽም የድርጅቶቹን አነሣስም ይሁን ዓላማ ጨርሶ ያላጤነ፣ ታሪክንም ያላገናዘበ ሌላው የተዛባ ስሌት ነው:: የተወሰኑ ኃይሎች ያውም ጫና ለማሣደርና አሣብን ለማስቀየር ምንም ዓይነት ተጨባጭ የማስገደጃም ይሁን ተፅዕኖ ማሣደሪያ አቅም ሣይያዝ እንደዚኽ ዓይነት አስተሣሰብ ምኞታዊ፣ ከምኞታዊው ያውም ተላላ ከመሆን አያልፍም::

ሕወሓት ኢሕአፓና የኢዴኅ ላይ ጦር የሰበቀው ሌላው ቀርቶ "የጋራ ጠላት" የሆነውን ደርግ በጋራ ለመዋጋት ሣይቻል ቀርቶ አይደለም:: ቢያንስ በኢሕአፓ በኩል *"የብሔር ጥያቄ የዴሞክራሲ ጥያቄ ነው"* በሚል ፍልሥፍና አሉ የተባሉ ልዩነቶችን በውይይት ለመፍታት ሲማስን በሕወሓት በኩል ግን ኃይሉን ማደራጀትና በቂ ኃይል ሲያገኝ ጦርነት ማድረግን ነው የመረጠው:: ለምን ቢሉ ሁለቱ በተመሣሣይ ወቅት በአንድ ቦታ ተቻችለው መቀጠልና እኩል ማደግ የማይቻል ስለሆነ ነው:: ኢሕአፓም ሆነ ኢዴኅ በትግራይ ላይ ያላቸውን ይዞታ እያጠናከሩ መሄድ ማለት የሕወሓትን የሰው ኃይልም ይሁን ሌላ የድጋፍ ምንጫቸውን የሚያደርቅ ስለሚሆንና ለነሱም እንደ-ድርጅት ለመቀጠል (ለመኖር) ያላቸውን ምክንያት የሚያሣጥርና አስፈላጊነትም የሚሸር ስለሚሆን በቀጥታ የነሱን ኅልውና የሚፈታተን ነበር:: ስለዚኽ የአንዱ መኖር በሌላው መጥፋት ላይ መውደቁ የግድ ነበር:: ይኽን ደግሞ ከኢሕአፓና ከኢዴኅ ይበልጥ የተረዳው ሕወሓት ነበር:: በሁለቱ ድርጅቶች በኩል ግን የሕወሓት በትግራይ መኖርና አለመኖር ይኽን ያኽል ለኅልውናቸው ጠር አድርገው የማያዩበት ምክንያት ግልጥ ነበር:: እንግዲኽ ሁለቱ የታጠቁ ክፍሎች (ኢሕአፓና ኢዴኅ) በ"መቅረብ" እና አብሮ ለመሥራት በመሞከር ሕወሓትን ከቆመበት አንዲትም ጋት "ወደ-መኻል" እንዲመጣ ማድረግ እንዳላስቻለ እየታወቀ፣ በምን ተአምር ባዶ-እጁን ያለ ግንቦት ሰባት ይሁን ሌላ ኢትዮጵያዊ ኃይል እነዚኽን ቡድኖች ያውም ኋላ "የራሣቸው ቦታ" ላይ የመቆናጠጥ ዕድል ሲያገኙ የተመሠረቱበትን፣ የታገሉበትንና የሚታገሉበትን አሣብ የሚቀይሩት? እንኳን ሊቀይሩ እንደ-ሸዓብያና ወያነ "ብቅልፂምና" ከማለት ውጭ ለተደረገላቸው ለጋስ አስተዋፅዖ እውቅና እንኳን እይሰጡም:: ምን በወጣቸው!! የታገሉት ለዚያ "ወደ-መኻል" እንዲመጣ ለሚፈለግ ዓላማ እኮ አይደለም:: ማንስ በነሱ ቦታ ቢሆን ይኽንን ያኽል ጊዜ ታግሎ ከዚያ መስዋዕትነት ከከፈለበት ግብ ያነሰ ለማግኘት ሊፈልግ ይችላል? ስለሆነም ዴሞክራትና የአንድነት ኃይሉ አንድነቱን አጥቶ ስብጥርጥር ባለበት ሁኔታ ከነዚኽ ታጣቂ ኃይሎች ጋር የሚደረግ "ትብብር" የእነሱን አጀንዳ ከማሣካትና አጃቢ ከመሆን ሌላ ውጤት አይኖረውም::          ***ይቀጥላል....***